# <u>የፖርትላንድ ም/ቤት አባላት 60 ሺህ ዶላር ቦንድ ገዙ</u>

የፖርትላንድ ታላቁ የሕዳሴ ም/ቤት አባላት እ.ኤ.አ ጁን 9/2013 ባካሄዱት ስብሰባ ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል 60 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ቦንድ ገዙ። በስብሰባው ላይ በቁጥር 50 የሚሆኑት የም/ቤቱ አባላት ተሳትፈዋል።

ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ በሎስአንጀለስ የኢፌድሪ ቆንስል ጄኔራል በም/ቤቱ ስብሰባ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የታላቁ ሕዳሴ ግድብን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ጠቀሜታና እንዲሁም ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ የገለፁ ሲሆን፣ የፖርትላንድ ም/ቤት ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ ድጋፍ በማሰባሰብ ረገድ እያደረገ ያለውን አርአያነት ያለውን አስተዋፅኦ በማድነቅ፣ ግድቡ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የም/ቤቱ አባላት የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የም/ቤቱ የሥ/አ/ኮ አባልና የእለቱን የስብሰባ መድረክ የመሩት አቶ ተመስገን በሪሶ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ጠላት የሆነውን ድህነትን ለመቅበር ወሳኝ ድርሻ ያለውን የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታን ዳር ለማድረስ ሁሉም ወገኖች የበኩላቸውን ለማበርከት እንዲረባረቡ ጥሪ አድርገዋል።

የም/ቤቱ ም/ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ተሻለ ተስፋ ገ/የሱስ ባደረጉት ንግግር የዕለቱ ስብሰባ ዋና ዓላማ በቀጣይ በስፋት ለሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ ም/ቤቱን ለማጠናከር ሲባል መካሄዱንና ከዚሁ ጎን ለጎን የፈንድሬዝንግ ሥራ ማካሄድ መሆኑን ገልፀው፣ የም/ቤቱ አባላት ከስብሰባው በሚያገኙት ግንዛቤ አቅማቸውን አጠናክረው ለቀጣዩ ወሳኝ የፈንድሬዝንግ ዝግጅት እንቅስቃሴ ለማድረግ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ጥሪ አድርገዋል።

የም/ቤቱ ፀሀፊ የሆኑት አቶ ገሠሠ ገ/ሥላሴ ባደረጉት ንግግር ም/ቤቱ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ያከናወንዋቸውን ተግባራት በመዘርዘር ከእነዚህ ውስጥ በተለይም ሥ/አ/ኮ አባላት በቅድሚያ ቦንድ በመግዛት ለሌሎች የም/ቤት አባላት አርአያ በመሆን መንቀሳቀሳቸውን ገልፀው፣ በመቀጠልም የቀድሞው የኢፌድሪ ጠ/ሚ/ር የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ አስደንጋጭ ዜና እረፍትን ተከትሎ የፖርትላንድ ከተማ አስተዳደር በየዓመቱ ስፔተምበር 2 የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መታሰቢያ ቀን ሆኖ እንዲከበር እንዲወሰን ም/ቤቱ በስኬታማነት መንቀሳቀሱን ገልፀዋል። በማያያዝም ም/ቤቱ መደበኛ የፈንድሪዚንግ ዝግጅት ባያካሂድም በከተማው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ት/ኢትዮጵያውያንን በማነቃነቅ በዕለቱ የተገኘውን ገቢ ጨምሮ በጠቅላላው 152,500 የአሜሪካን ዶላር ቦንድ መሸጡን ገልፀው ፣ የም/ቤቱ አባላት በቀጣይ ለሚካሄደው የፈንድሬዚንግ ሥራ እንዲዘጋጁ ጥሪ አድርገዋል።

የም/ቤቱ አባላት ከገለፃዎቹ በኋላ ጥያቄና አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ ያደረጉት ሲሆን፣ ምላሾችም በክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ፣ በምክትል ቆንስላ ጄኔራል በአቶ ኢሳያስ ጎታ እና በሥ/አ/ኮ አባላት ተሰጥትዋል። በመጨረሻም የም/ቤቱ አባላት በቅርቡ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ቦንድ ሽያጭ ፈንድሬዝንግ መድረክ ለማዘጋጀት የተስማሙ ሲሆን፣ ይህንን ስኬታማ ለማድረግ በተደራጀ አኳኋን ለመንቀሳቀስ ቃል በመግባት የዕለቱን ስብሰባ አጠናቅቀዋል።